https://www.path-2-happiness.com/am

የሰውን ተፈትሮ መጻረር ፦ ምድራዊ ሰው ሠራሽ ሃይማኖቶች የሰውን ተፈጥሮ በመጻረር የማይችለውንና የማገባውን በማሸከም ላይ የተመሰረቱ፣ሰብአዊ ተፈጥሮንና ጤናማ አእምሮን በመቃረን የቆሙ፣ተከታዮቻቸው ከቀጥተኛው መንገድ ርቀው ያፈነገጡ ናቸው። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{فَأَقِمْ وَجْهَكَ لِلدِّينِ حَنِيفًا ۚ فِطْرَتَ ٱللَّهِ ٱلَّتِى فَطَرَ ٱلنَّاسَ عَلَيْهَا ۚ لَا تَبْدِيلَ لِخَلْقِ ٱللَّهِ ۚ ذَٰلِكَ ٱلدِّينُ ٱلْقَيِّمُ وَلَٰكِنَّ أَكْثَرَ ٱلنَّاسِ لَا يَعْلَمُونَ ﴿٣٠﴾}[الروم: ٣٠]

‹‹ወደ እውነት ተዘንባይ ኾነህ ፊትህን ለሃይማኖት ቀጥ አድርግ፤የአላህን ፍጥረት ያችን አላህ ሰዎችን በርስዋ ላይ የፈጠረባትን (ሃማኖት ያዙዋት)፤የአላህን ፍጥረት መለወጥ የለም፤ይህ ቀጥተኛ ሃይማኖት ነው፤ግን አብዛኛዎቹ ሰዎች አያውቁም።››[አል ሩም:30]

አፈተረቶችና የቅዠት ሀሳቦች ፦ እነዚህ ምንም ዓይነት አእምሯዊ ሎጂካዊም ሆነ ሳይንሳዊ መነሻ ሳይኖራቸው በባዶ ቅዠት ላይ የተመሰረቱ እምነቶች ወይም አስተሳሰቦች ናቸው። ምድራዊ ሃይማኖቶች አንዳች ማስረጃም ሆነ መሰረት በሌላቸው ተራ የቅዠት ሀሳቦች የተሞሉ ሲሆን ብቅዠት ላ ሊመሰረት የሚችለው ቅዠት ብቻ ነው። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{قُلْ هَاتُوا۟ بُرْهَٰنَكُمْ إِن كُنتُمْ صَٰدِقِينَ ﴿٦٤﴾}[النمل: ٦٤]

‹‹እውነተኞች እንደኾናችሁ አስረጃችሁን አምጡ፣በላቸው።››[አል ነምል:64]

እርስ በርሳቸው መጣረስ ፦ ሰው ሠራሽ እምነቶች በቅራኔዎች የተሞሉ፣እያንዳንዱ ቡድን ከተቃረነውና ከአብራኩ ወጥቶ በተሸሻለው ሌላው ቡድን ውድመትና ፍርስራሽ ላይ የተመሰረቱ ናቸው። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَلَوْ كَانَ مِنْ عِندِ غَيْرِ ٱللَّهِ لَوَجَدُوا۟ فِيهِ ٱخْتِلَٰفًا كَثِيرًا ﴿٨٢﴾}[النساء: ٨٢]

‹‹ከአላህ ሌላ ዘንድ በነበረ ኖሮ፣በርሱ ውስጥ ብዙን መለያየት ባገኙ ነበር።››[አል ኒሳእ:82]

መለኮታዊ ሃይማኖቶች ግን፣የአላህን ቃልና መልክቱን ያደርሱ ዘንድ መልክተኞችን በመላክ ሊመራቸውና መንገዱን ሊያበራላቸው፣ከከንቱነትና ከመዋለል፣ከአፈተረትና ከማጋራት፣የሰውን ተፈጥሮና ሰብአዊ አእምሮን ከመጻረር ሊያርቃቸው ከአላህ ለሰው ልጆች የተቸሩ ጸጋዎቹ ናቸው።

{رُّسُلًا مُّبَشِّرِينَ وَمُنذِرِينَ لِئَلَّا يَكُونَ لِلنَّاسِ عَلَى ٱللَّهِ حُجَّةٌۢ بَعْدَ ٱلرُّسُلِ ۚ وَكَانَ ٱللَّهُ عَزِيزًا حَكِيمًا ﴿١٦٥﴾}[النساء: ١٦٥]

‹‹ከመልክተኞቹበኋላለሰዎችበአላህላይአስረጅእንዳይኖር፣አብሳሪዎችና አስፈራሪዎች የኾኑን መልክተኞች (ላክን)፤አላህም አሸናፊ ጥበበኛ ነው።››[አል ኒሳእ:165]





## የቡድሂዝም መጣረስ

‹‹ቡድሂስቶች ወይም ከፊሎቻቸው የአምላክን መኖር ሲያስተባብሉ፣ቡድሃን የአምላክ ልጅ ነው ይላሉ። መንፈስ መኖሩንም ሲያስተባብሉ የሙታን ነፍስ በሌላ ፍጡር አካል ትመለሳለች ብለው ያምናሉ። ››